# ምዕራፍ ሰባት

# የአረጋውያን ሚና

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተ-ነገር ትሠራላችሁ።
- ✓ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋትን ተጠቅማችሁ ስዕላዊ ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- ✓ ድርብና ነጠላ ትዕምርተ - ጥቅሶችን በተገቢ ቦታ ትጠቀማላችሁ።
- ✓ አባባሎችን፣ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን ሰብስባችሁ ትርጉማቸውን ታብራራላችሁ።
- ✓ ከተለያዩ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሐሳቦች በግለ ገለጻ ታቀርባላችሁ።
- ✓ የግጥማዊ ስነ-ቃሎችን ሐሳብ ለይታችሁ ትገልጻላችሁ።
- ✓ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ታደርጋላችሁ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች፣ አረጋውያን የሚባሉት የማህበረሰብ ክፍሎች በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ይመስላችኋል?
2. አረጋውያን በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ምን ዓይነት የጎላ ተሳትፎ አላቸው?

## "መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን"

“ዕድሜ መስታወት ነው።” ይህ አባባል፣ ሰዎች እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ ከህይወት ያካበቱት ልምድና እውቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነው።

አረጋውያን ከህይወት ብዙ የተማሩ፣በአያሌ የኑሮ ውጣ ውረዶች ተፈትነው ያለፉ የእድሜ ባለጸጎች ናቸው። ከህይወት ልምዳቸው ጥቂት በጨለፍን ቁጥርም ሚዛን የሚደፋ ቁም ነገር አናጣም።

አረጋውያን በዕድሜ መግፋት የተነሳ አካላዊ ቅልጥፍናቸው እየደከመ ቢሄድም እንኳ አቅማቸው በፈቀደው መጠን በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው ልናገኛቸው እንችላለን፤ ይሁን እንጂ፣ በዚህ እድሜያቸው በማህበረሰቡ ጎልቶ የሚታየው የጉልበት ተሳትፏቸው ሳይሆን አእምሮአዊ ሀብታቸው ነው። አረጋውያን ታዳጊዎችን ስነ ምግባር በማስተማርና በመምከር፣ በግለሰብ መካከል ይሁን በቡድን የሚፈጠሩ ግጭቶችን በማርገብና በመሸምገል በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ክስተቶችን ለአዲሱ ትውልድ በመንገር ታሪክን የማስተላለፍና የመመስከር ከፍተኛ ሚና አላቸው።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ተማሪዎች ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀፆች ምን ተረዳችሁ?

በተለይ ተከታዩን ትውልድ ከመምራትና ቀና መስመር ከማስያዝ አኳያ ያላቸውን ድርሻ ስንመለከት፣ “መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን” የሚለውን ብሒል እንድናነሳ ግድ ይለናል፡፡ አረጋውያኑ የመምከርና የማስተማር ሚናቸውን የሚጫወቱት በዘዴና በማዋዛት ሲሆን፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃዎችም እድሜ ጠገብ የስነ-ቃል ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ተረት፣ ቅኔ፣ ቃላዊ ግጥም፣ እንካስላንቲያ … በሳል ሀሳብ የሚያስተላልፉ ጥበቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ስነ-ቃሎች ወጣቶች ወደ ጥፋት እንዳይገቡና አስቀድመው እንዲጠነቀቁ ይመክራሉ፡፡ አንዴ የተፈጸመን ጥፋት ማብሰልሰል ዋጋ እንደሌለውም ይናገራሉ፡፡ የይቅርታን ትልቅነት ይሰብካሉ፡፡ ስንፍናን ይኮንናሉ፤ ጉብዝናን ያበረታታሉ፡፡ ንፉግነትንና ስግብግብነትን ይነቅፋሉ፤ ክፋት ምቀኝነትን ያወግዛሉ፡፡

ለምሳሌ የመተባበርን ጠቀሜታ፡- “ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች፡፡” በማለት ለዛ ባለው ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ "ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል” በሚል አባባል ችኩልነትን ይቃወማሉ፡፡

በቃላዊ ግጥሞቻቸው ጎበዙን፡-

የበሬው ቄስ የበሬው መምህር፤
አቆላላፊ ክምር ለክምር ፣
ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው፣
ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡” እያሉ ያሞካሻሉ፡፡

ሰነፉን ደግሞ፡-

“አንድ ወር አይበቃውም አንድ ዓመት ያረሰው
እንኳን ቤተሰቡ ጎተራው ወቀሰው፡፡” በማለት ያንኳስሳሉ፡፡

አረጋውያን እድሜ አዋቂነትን አጎናጽፏቸዋል፡፡ “አንድ አረጋዊ ሲሞት አንድ ቤተ መጻሕፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል” የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ አረጋውያን ሰናይ ተግባራትን ተመልክተው ይመርቃሉ፡፡ እኩይ ተግባራትን ታዝበው ያወግዛሉ፡፡ ማህበረሰቡም ይህንኑ በዕድሜና በልምድ ያላቸውን የመሪነት ብቃት ተቀብሎ ያከብራቸዋል፡፡ “የሚያድግ ልጅ

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

አይጥላህ፤ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ" የሚለው አባባል ከላይ ካነሳነው የአረጋውያንን ምክርና ቃል ከማክበርና ከመፈጸም ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዜጎች ማህበረሰቡን በመምራትና በመቆጣጠር በኩል ያላቸውን ሚና ትልቅ ግምት በመስጠት ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ምንድነው?

ለ. ማህበረሰባችን ለአረጋውያኑ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? በማስረጃ በማስደገፍ አብራሩ፡፡

ሐ. ስነ ቃሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

መ. በወጣቶችና በአረጋውያን መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

ሠ. ከምንባቡ ሐሳብ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋውያንና ያልተማሩ አረጋውያን በማህበረሰቡ ያላቸው ተቀባይነት እንዴት ዓይነት ይመስላችኋል? በእኩል ዐይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፉ፡፡

**፪. የሚከተሉት አባባሎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ የሚያስተላልፉትን መልዕክት አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡**

| | |
|---|---|
| ሀ. ሚዛን የሚደፋ | መ. አዕምሮአዊ ሀብት |
| ለ. የእድሜ ባለፀጋ | ሠ. መሸምገል |
| ሐ. የኑሮ ውጣ ውረድ | ረ. ሰናይ ተግባር |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል ሁለት፣ መናገር

፩. በአካባቢያችሁ ያሉ አረጋውያን በልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች /በእድር፣ በቀበሌ፣ ስብሰባ፣ በክብረ በዓላት … /ላይ በመገኘት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሲናገሩ ምክር ሲሰጡና ሲወያዩ ያጋጥሟችኋል፡፡ ይህንን በመፈለግና በመጠቀም አረጋውያኑ በንግግራቸው፣ በጭውውታቸው እንዲሁም በውይይታቸው ያስተላለፉትን መልዕክት ተከታትላችሁ ያገኛችሁትን ፍሬ ሐሳብ አሳጥራችሁ ክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ፡፡

፪. በአካባቢያችሁ ያሉ አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አስተዋፅኦ አስመልክታችሁ ያያችሁትን፣ ያነበባችሁትን ከሰዎች ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ ካጠናቀራችሁ በኋላ ክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡ፡፡

፫. በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ በቀረበው ምንባብ፡-

- ስነ ምግባር ማስተማር፣ መምከር፣
- ግጭትን ማርገብ፣ ማስታረቅ፣
- ታሪክን ለትውልድ ማስተላለፍ፣ …

ዋና ዋና ተብለው የተጠቀሱ የአረጋውያን ተግባራት ናቸው፡፡ እናንተም በቡድን በመከፋፈል ከሚናዎቹ አንዱን በመምረጥ ንግግር አዘጋጅታችሁ በመረጣችሁት የቡድን መሪያችሁ አማካይነት ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

፬. የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር የሚደረገው፣ ሰዎችን ለአንድ ተግባር ለማነሳሳት፣ ለማግባባት በመጨረሻም በተግባር /በድርጊት/ ለማሳተፍ ነው፡፡ አረጋውያን የአካባቢውን ህዝብ በሥራ ለማስማራትና ማህበራዊ ችግር ለመፍታት የተለያዩ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግሮችን፣ አባባሎችን ይጠቀማሉ፡፡ ንግግሮቹ በግጥም፣ በምሣሌያዊ አነጋገር … ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች እናንተም አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቀሟቸውን አባባሎች በመረጃነት በመጠቀም በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር አዘጋጅታችሁ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፤ ሰዋስው

### የቃላት ቀጥተኛ ፍች

የቃላት ቀጥተኛ ፍች የምንለው መዝገበ - ቃላት ላይ ሰፍሮ የምናገኘውን የቃሉን ፍች ነው።

የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ቀጥተኛ ፍች በምሳሌነት ተመልከቱ!

- አዛውንት → ሽማግሌ ወይም አሮጊት
- ወፈረ → አካል ጨመረ፤ ደነደነ፤ ሰባ፤ ግዙፍ ሆነ፤ ለደለደ
- ማገጠ → ባለገ፤ ተበላሸ፤ ዋልጌ ሆነ
- ቀጠሮ → አንድ ነገር ለመስራት’ ለመገናኘት የሚደረግ የቦታ፤ የጊዜ ውሳኔ

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍች ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ አስፍሩና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

| | |
|---|---|
| ሀ. ትንቢት:____________ | ረ. መባቻ:____________ |
| ለ. ፋና:____________ | ሰ. በለተ:____________ |
| ሐ. ሁዳድ:____________ | ሸ. አበጀ:____________ |
| መ. ኩርባ:____________ | ቀ. ዘበተ:____________ |
| ሠ. ህዳሴ :____________ | በ. አለመ:____________ |

**፪. ከአረጋውያን ጋር ተያያዥነት ያላቸው አምስት ቃላት ከመዝገበ ቃላት ከነፍቻቸው አምጥታችሁ ክፍል ውስጥ አንብቡ።**

**፫. ምሳሌውን ከተመለከታችሁ በኋላ ከታች ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች በመስጠት በቃሉ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ዓረፍተ-ነገር ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።**

**ምሳሌ:-** ደፈረሰ → ተመሳሳይ ፍች = ተበጠበጠ ፣ ታወከ ፣ ተሸበረ
→ ተቃራኒ ፍች = ጠራ ፣ ተረጋጋ

ሀ. ሠፈር ውስጥ በተነዛው ወሬ የቤተሰቡ ሰላም ታወከ።
ለ. ፖሊሶቹ ፈጥነው በመድረሳቸው ገበያው ተረጋጋ።

© MoE, FDRE Not to be republished

| | | |
|---|---|---|
| 1. ተቸ | 3. አፈሰ | 5. ገነባ |
| 2. አገደ | 4. ነፈገ | 6. አደፈ |

**፬. ከዚህ በታች የቀረበው አጭር ጽሑፍ ድርብና ነጠላ የጥቅስ ምልክት ይጎድሉታል፡፡ አስቀድማችሁ በተማራችሁት የጥቅሶች አገልግሎት መሠረት የጥቅስ ምልክቶቹን በተገቢ ቦታ በማስገባት አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

ዙሪያዋን የከበቧት ሰዎች ስለምን እያወሩ እንደሆነ ቢገባትም እንዳ ልሰማችና እንዳልገባት ለመሆን ሞከረች፡፡ በፊርጥ የተንቆጠቆጠው ነጭ የሙሽራ ልብሷ ሰውነቷን አለቅጥ ወጥሮ አስጨንቋታል፡፡ የዛሬን አያድ ርገውና እናቷ የእኔ ልጅ ወገቧ እኮ ችቦ አይሞላም እያሉ የሚያሞግሱት ሽንቃጣ ቁመናዋ በድብኝት መሳይ ቅርፅ ተተክቷል፡፡ ሁሉ ነገር አስጠላት የጎረቤት መጠቋቆሚያ መሆኗ አበሳጫት፡፡

ተው ይሄ ሠርግ ይቅርብን ብለው እናትሽ ሰው አያደርጉኝም ብሎ ጉድ ያደረገኝ አቶ ደረጀ ነው በማለት በባሏ ክፉኛ ተብሰከሰከች፡፡ ወዲያው አንደኛ ሚዜዋ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብላ ደረጀ ወደ ቤት እየቀረበን ነው ፎቶ ግራፍ አንሺውም ተዘጋጅተሽ ጠብቂኝ ብኋል ብሎ ደውሎ ነበር አለቻት፡፡ ሙሽሪትም በታከተ አንደበት አያቴ ድሮ እዩኝ እዩኝ ለደብቁኝ እያለች ስትተርት አይገባኝም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ይኸው ትርጉሙ ግልጽ ሆነልኝ በማለት ብሶቷን አሰምታ ፊቷን በነጭ መሀረቧ ማባበስ ጀመረች፡፡

## ክፍል አራት፡ ስነጽሑፍ

### ስዕላዊ ድርሰት

ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ምስልና ገጽታ በቃላት አማካይነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር የድርሰት ዓይነት ነው፡፡ በዚህ የድርሰት ዓይነት ደራሲው የሚጠቀምባቸው ቃላት በሰው አእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

አምሳሉና ደምሴ (1982፡ 130) ስዕላዊ-ድርሰትን ሲገልጹት “ያንድን ነገር ሁናቴ በዓይን እንዳዩት በእጅ እንደዳሰሱት በጆሮ በቅርብ ሆነው እንደሰሙት በጠቅላላው ግዙፍ አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት ዓይነት ነው” ይላሉ፡፡

© MoE, FDR... Not to be rep...

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት**

ለጠረጴዛው ጎኗን ሰጥታ እግሮቿን አነባብራ ተቀምጣለች፡፡ ክንዷን ጠረጴዛው ላይ አስደግፋ መዳፏ ላይ ጋደም ብላለች፤ አውራ ጣቷ ክብ አገጯ ስር ገብቶ በሌባ ጣቷ ጉንጯን እንደማከክ እያለች ትተክዛለች፤ሀሳብ የያዘው ወይም የተገረመ ሰው ትመስላለች፡፡

ጥቁር፤ የሚያብለጨልጭ ቀሚሷ የሻማውን መብራት ሲስብ ፤ እንደ አልማዝ የሚያበራው ጉትቻዋ መልሶ ይወረውረዋል፡፡ በተለይ የወርቅ ቀለም ካለው ነጠላ ጫማዋ ውስጥ ለብቻው ሾልኮ ወጥቶ የሚታየው አውራ ጣቷ የባለጌ ልጅ ምላስ ይመስል በሰው ላይ ያሾፋል፤ ይቀልዳል፡፡ *(በዓሉ ግርማ 1962፣ 37)*

**፩. በአካባቢያችሁ የሚገኘውን የገበያ ስፍራ ሁኔታ ከላይ የተሰጠውን የስዕላዊ ድርሰት ማብራሪያን መሠረት አድርጋችሁ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ወይም ሐረጋትን በመጠቀም ከሶስት አንቀጽ ያልበለጠ አንድ ስዕላዊ ድርሰት ጽፋችሁ ክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡**

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ምሳሌያዊ አነጋገር በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሠረት የሚፈጠር በቁጥብና በምርጥ ቃላት በአጭሩ የሚነገር የተጨመቀ ጥልቅ ሐሳብን የያዘ የስነ-ቃል ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌያዊ አነጋገር ለሀሳብ መቋጫ፣ ማጠናከሪያ፣ ማጉሊያና ግልጽ ማድረጊያ ይሆናል፡፡ ሰዎች በንግግራቸው ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ሀዘን-ደስታቸውን፣ ስለህይወት ያላቸውን አመለካከት ያንጸባርቁበታል፡፡ እምነታቸውን ይገልጹበታል፡፡ በተጨማሪ ቅሬታቸውን የሚያሳውቁበት አስነዋሪ ተግባርን የሚነቅፉበት መልካሙን የሚያሞግሱበት እጥር ምጥን ያለ የሀሳብ መግለጫ ነው፡፡

/ዘሪሁን አስፋው፣ 1992፣ 35፡36/

የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡-

* ስግብግብነትን የሚነቅፉ፣
  - "ሆዳም ቢፈተፍት የበላ ይመስለዋል፤"

* የምቀኝነትን መጥፎነት የሚነግሩ፡-
  - "ምቀኛ ጠላቱን ይተክል ወዳጁን ይነቅል፤"
* ላለፈ ነገር መቆጨት ትርጉም እንደሌለው የሚመክሩ፡-
  - "ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፤"
* ችግር ሳይጠና በጊዜ መፍትሔ መፈለግ ግድ መሆኑን የሚነግሩ፡-
  - "አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው"፡፡
* ብቻ መልፋት ውጤታማ እንደማያደርግ የሚነግሩ
  - "አንድ ጣት ቀንጫ አይገድልም፤"

**፪. ቀጥሎ የተሰያዩ ገጠመኞች በትረካ መልክ ደቀርቡላችኋል፡፡ በትረካው የቀረቡትን ዐውዶች በመመርመር ተስማሚ ምሳሌያዊ አነጋገር በመፈለግ ባዶ ቦታውን አሟሉ፡፡**

1. አቶ መፍትሔ ቸር ሰው ናቸው፡፡ ሰው በልቶ የሚጠግብ ጠጥቶ የሚረካ አይመስላቸውም፡፡ ይህንን ቸርነታቸውን ያወቀ ሁሉ ታዲያ ቤታቸውን ሳይረግጥ አይውልም፡፡ ጥግነህ የአቶ መፍትሔ ወዳጅ ሆኖ ቤታቸው ገባ ወጣ ማለት ከጀመረ ወራትን አስቆጥሯል፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀንም በልቡ ሲያውጠነጥነው የከረመውን ሐሳብ በተግባር ፈጸመው፡፡ አቶ መፍትሔ ዘመድ ሞቶባቸው ራቅ ወዳለ አካባቢ መጓዛቸውን አስተውሎ በረት ሙሉ ከብታቸውን እየነዳ ከአገር ጠፋ፡፡ አቶ መፍትሔ ጉዳቸውን ሲሰሙ __________ ብለው ተረቱ፡፡
2. ጥናቱን በጥሩ ሁኔታ ሠርተው ያቀረቡት ስለሺና ጌጤ ቢሆኑም ምስጋናና ክብር ያገኙት ግን አለቃቸው አቶ መኳንንት ናቸው፡፡ ለዚህ አይነቱ አጋጣሚ ________________ የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ተስማሚ ነው፡፡
3. በዘውዴና በባለቤቷ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እየከረረ በመምጣቱ በሽማግሌዎች እየታየ ነው፡፡ ዘውዴ የምትወዳት ጓደኛዋ ትብለጥም ከባለቤቷ ጋር መጋጨቷን ሰምታ ሁለቱን ለማስማማት ላይ ታች ማለት ጀምራለች፡፡ ይህንን የታዘቡ ጎረቤቷ እመት አረጋሽ _____________ብለው ተረቱባት፡፡

4. የአማርኛ መምህሯ የተማሪዎቻቸውን የቤት ሥራ ለመሰብሰብ ተዘጋጅተዋል። ከፊት የተቀመጡት ተማሪዎች የቤት ሥራቸውን ለማሳየት ፈጠን ብለው ሲያወጡ ከኋላ የተቀመጡት ልዕልትና መዲና ግን ከሳምንት በፊት የተሰጠውን የቤት ሥራ አሁን ለመሥራት ይንደፋደፉ ጀመር። ይህንን ያስተዋሉት መምህርትም የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ተናገሩ።
5. ሔኖክ ገንዘብ አያያዝ አታውቅም በሚል ሰበብ ከሁለት ዓመት ጓደኛው ተለያይቶ ሌላ የሴት ጓደኛ ይዟል። ሔኖክ እንደተመኘው አዲሷ ጓደኛው እንኳን ገንዘቧን በአግባቡ ልትይዝ የእሱንም በሰበብ አስባቡ ታጫርሰው ገባች። ሔኖክም የቀድሞ ጓደኛውን እያሰበ ____________ብሎ በራሱ ላይ ተረተ።

**፫. ከተከታዮቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁለቱን በመምረጥ ሲነገሩ የሚችሉበትን ዐውድ ፈጥራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

1. በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል።
2. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ።
3. ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል።
4. አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይጸጸቱ።
5. ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም።

**ቃላዊ ግጥሞች /ሽለላና ፉከራ/**

ቃላዊ ግጥም አመንጪው (ደራሲው) በትክክል አይታወቅም። ስለዚህ ባለቤቱ ህዝብ ነው። በቃል ተደርሶ በቃል ሲከወንና በቃል ሲተላለፍ የኖረ ጥበብ ሲሆን፣ ከዜማ ጋር በዘፈንና በእንጉርጉሮ ይከወናል።

ቃላዊ ግጥሞች በሰርግ፣ በክብረ በዓላት፣ በሙሾ፣ በስራ ቦታ፣ በልጆች ጨዋታ፣ በጦርነት ወቅት … ላይ ይደረደራሉ፤ ይዜማሉ። ይዘታቸው የፍቅር፣ የጥላቻ፣ የናፍቆት፣ የትዝታ፣ የብሶት፣ የንቀት የሙገሳ … ሊሆን ይችላል።

ሽለላና ፉከራ የሚከወኑበት አጋጣሚና የሚከወኑበት ዓላማ አንድ ሆኖ በአቀራረባቸው ግን የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው የቃላዊ ግጥም ዘርፍ ናቸው።

© MoE, FDR… Not to be rep…

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ብዙውን ጊዜ የሚከወኑት ማህበረሠቡን ለማነሳሳት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ነው፡፡ በሚከወኑበት ጊዜ ከዋኙን እንዲሁም አድማጩን /ተመልካቹን/ በስሜት በመሙላት አካሉና አእምሮው እንዲበረታና በሀሴት እንዲሞላ ከዚያ አልፎ በወኔ እንዲነሳና ለዓላማውም እንዲጸና ያደርጋሉ፡፡

አከዋወናቸውን በተመለከተ ሽለላ በዜማ በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ /ክራር፣ ማሲንቆ፣ ዋሽንት /ታጅቦ የሚቀርብ ሲሆን ፉከራ ግን በቃል ንባብ መልክ የሚቀርብ ነው፡፡

በሁለቱም ውስጥ ያሉ ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ጀግናን፣ደፋርን የሚያወድሱ፣ የሀገርን ፍቅርና ክብር የሚሰብኩ፣ ፈሪና ሰነፍን የሚኮንኑ ናቸው፡፡ ሽለላና ፉከራ ወኔ በመቀስቀስ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ስነ ቃሎች ናቸው፡፡

**፬. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ሐሳብ በዋናነት በመመርመር የፍቅር፣ የሙገሳ፣ የጥላቻ፣ የንቀት፣ የነቀፋ፣ የብሶት... እያላችሁ መልሱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** "እንጎራጉራለሁ የደላኝ መስዬ፣
ሌሊቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብዬ፡፡" /ብሶትን የሚገልጽ/

1. ገዳይ በየበሩ በየሸንተረሩ
   ይፈለግ የለም ወይ የአዳኝ ውሻ ዘሩ፡፡
2. የእገሊት ወዳጅ ጭራሽም ልብ የለው፣
   የወንድሙ ሬሳ ወድቆ የከረመው፣
   ልብማ ቢኖረው ደሙን ይመልሳል፣
   በግንባሩ ደፍቶ አንጀቱን ያርሳል፡፡
3. ከሳሽን ጠቆርሽን ይለኛል ባላገር፣
   የሆዴን አውጥቼ ለስንቱ ልናገር፡፡
4. የሳር ውስጥ መንገድ ይመስላል ወገቡ፣
   መቼ ያስታውቃል ራቡ ጥጋቡ፡፡

5. ልብ አልባ ነበር የሴት ወይዘሮ እቃ፣
   ወርቅ እንቁ ነበር የሴት ወይዘሮ እቃ፣
   አወይ የኔ ነገር ሄደች ልቤን ታጥቃ፡፡

6. በበጋ እንዳያርስ ፀሐይ እየፈራ፣
   በሐምሌ እንዳያርስ ዝናብ እየፈራ፣
   ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ፡፡

7. እንደገንቦ ጠላ ብትንደቀደቂ፣
   እንደ ጓሮ ጎመን ብትንከረፈፊ፣
   ወደደኝ ወደድኩት እንግዲህ እረፊ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥቅስ ምልክቶች ነጠላ (‹ ›) እና ድርብ (" ") ተጠቅመን መልመጃዎችን ሠርተናል:: ስዕላዊ ድርሰት የአንድን ነገር ገጽታና ምስል በቃላት አማካይነት ስሉ ለማቅረብ የሚሞከር የድርሰት ዓይነት እንደሆነ ተመልክተናል:: ሽለላና ፉከራ በግጥም የሚቀርቡ ወኔ ቀስቃሽ የስነቃል ዓይነቶች መሆናቸውን አይተናል:: የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ሰጥተናል:: የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት እንዲሁም ሀረጋት አገልግሎትን ተገንዝበን በተግባር ተጠቅመንባቸዋል:: የጽሑፍ ንግግርን አዘጋጅተናል:: ለተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች መስጠት ችለናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የነጠላ (‹ ›) እና የድርብ (" ") ጥቅስ ምልክቶችን አገልግሎት በአጭሩ ጻፉ::
2. አንድን ጭውውት ወይም ንግግር አዳምጦ ማስታወሻ ለመያዝ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. ስዕላዊ ድርሰት በምን ዓይነት ስልት የሚቀርብ ድርሰት ነው? በአጭሩ አብራርታችሁ ጻፉ::
4. ሽለላና ፉከራ መቼ፣ ለምን ዓላማ ይከወናሉ? አጠር አድርጋችሁ ግለጹ::
5. የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር የሚያደርግ ሰው ንግግሩ ተቀባይነት እንዲኖረው ምን ማድረግ አለበት?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስቀረቡልኝ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የድርብና ነጠላ ጥቅስ ምልክቶች አገልግሎት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት አገልግሎት ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | የጽሑፍ ንግግር ለማዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቄአለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የስዕላዊ ድርሠት አጻጻፍን በመረዳት እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ፍች መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7. | የሽለላ፣ የፉከራ ቃላዊ ግጥሞች ባህሪይ እና አከዋወን ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished